የኢትዮጵያ ደረጃ

desalege

Digitally signed by desalege
DN: cn=desalege, o=ESA, ou=standard development, email=desalegne46@gmail.com, c=ET
Date: 2020.10.12 11:58:46 +03'00'

# ኢደ 6663:2021

የመጀመሪያ ዕትም

xx-xx-2021

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

## የወተትና የወተት ተዋጽኦ መሸጫ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት

ICS:xx .ÈÈ.

Published by Ethiopian Standards Agency

©ESA

## መቅድም (foreword)

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ንፅህና እና የጤና ነክ ተቋማትአገልግሎት ቴክኒክ ኮሚቴ (ቴኮ 205) ላይ መሰረት አድርጎ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው።

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ ኢ.ደ 6663:2021፤ የወተትና የወተት ተዋጽኦ መሸጫ የአካባቢ ጤና አጠባበቅ መስፈርት ሲሆን በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ አማካኝነት እንደ አዲስ የታተመ ነው።

የደረጃ መነሻ ሰነዱን ያቀረበው የጤና ሚኒስቴር ነው።ኤጀንሲያችን ለሰነዱ አቅራቢ ምስጋናውን ያቀርባል ።

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

## 1. ወሰን

ይህ የኢትዮጵያ ደረጃ በሁሉም ወተትና የወተት ተዋፅዖ መሸጫ ቤት ቤት የምግብ ደህንነት፤አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የንፅህና እና አካባቢ ጤና አጠባበቅ ያካተተ መስፈርት ነው፡፡

## 2. ማጣቀሻ

## 3. ቃላትና ትርገሜ

3.1

**የወተትና የወትት ተዋፅዖ መሸጫ ቤት**

በተፈጥሮ ከከብት (ከላም፣ከፍየል፣ ከግመል)የሚገኝ የተፈጥሮ ወተት ወይንም በወተት ማቀነባበሪያ ተቀነባብሮ በተለያየ መልክ የሚቀርብ የወተትና የወተት ተዋጽኦ መሰጫ ማለትነው ፡፡

3.2

**የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሶች**

የስራ ደህንነትና ንፅህና መጠበቂያ ቁሶች ማለት በስራ ቦታ ለሚከሰቱ ማንኛውም በንክኪ የጤና ችግር ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች ለመከላከል ሲባል የሚለበሱ/የሚደረጉ ቁሳቁሶች ናቸው፡፡

3.3

**የተሟላ እጅ መታጠቢያ**

ሙቅና ቀዝቃዛ የቧንቧ ውሃ፣ ፍሳሽ መቀበያ ከሴራሚክ (በብሎኬት/ግንብ) የተሰራ ገንዳ፣ ፈሳሽ ሳሙና፣ በሽታ አምጪ ተህዋሲያን ማጽጃና የዕጅ ማድረቂያ ሶፍትና የፍሳሽ መስመር የተዘረጋለት ማለት ነው፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

3.4.

**የውሃ አቅርቦት**

ከከተማው የውሃ መስመር ወይንም አግባብ ባለው አካል ተመርምሮ ለሰው ልጅ ጥቅም እንዲውል የተረጋገጠ የጉድጓድ ወይም ከሌሎች የውሃ መገኛ ምንጮች የተገኘ ውሃ ማለት ነው፡፡

3.5

**የመፀዳጃ ቤት**

ሰዎች በቁም ወይም በመቀመጥ  ከሰውነት የሚወጣ ቆሻሻ (አይነምደር እና ሽንት) የሚያስወግዱበት መቀመጫ፣በር፣ወለል ፣ግድግዳ እና ጣሪያ/ኮርኒስ ያለው ክፍል ነው፡፡

3.6.

**በቂ ብርሃን**

ማንኛውም ማየት የሚችልተጠቃሚየሚገለገልበትንክፍልአራቱንምጥጎችያለምንም ችግር ማየት የሚችልበት አካባቢ ማለት ነዉ ፡፡

3.7.

**ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ**

ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ፣ በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ፣ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት ቅርፁ አመቺ የሆነ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችል የቆሻሻ መሰብሰቢያ ማለት ነው፡፡

3.8

**የግል ንፅህና**

ሰው በራሱ ኃላፊነት በሽታ አምጪ ምቹ ሁኔታዎችን ለመከላከልና ጤናን ለመጠበቅ የራስንና የአልባሳት ንፅህና መጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራትን (ገላን መታጠብ፣ እጅን በሳሙና መታጠብ፣ አልባሳትን በንፅህና መያዝና ወዘተ) ማከናወን ማለት ነው ፡፡

3.9

**መጥፎ ሽታ**

በሰው ልጅ ማሽተቻ አካል ወይም አፍንጫ መጥፎ ስሜትን የማይፈጥር እና ለጤና ጠንቅ የሆነ መረን ነዉ፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD



©ESA

3.10

**የፍሳሽ ቆሻሻ**

ከድርጅቱ የተለያየ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች /ለምሳለሌ፡-ከመጸዳጃ፣ከእቃ ማጠቢያ ፣ከእጅ መታጠቢያ/ የሚወጣ የፈሳሽነት ይዘት ያለው ቆሻሻ ማለት ነው፡፡

# 4. መስፈርቶች

## 4.1 አጠቃላይ መስፈርቶች

4.1.1 የውሃና መብራት የመሰረተ ልማት አውታሮች የተሟሉለት መሆን አለበት፡፡

4.1.2 ድርጅቱ በሌላ የንግድ ዘርፍ ያልተያዘ በተደራቢም ሌላ ንግድ የማያካሂድ፣ ከመኖሪያ ቤትም ጋር ያልተያያዘና ራሱን የቻለ መሸጫ ቦታ መሆን አለበት፡፡

4.1.3 ህንፃው የተገነባበት ግብአት ልሙጥ የሆነ፣ በቀላሉ ሊፀዳ እና የእሳት አደጋን ሊቋቋም የሚችል መሆን አለበት፡፡

4.1.4 በድርጅቱ ክፍሎች በቂ የአየር ዝውውር መኖር አለበት

4.1.5 አገልግሎት ለመስጠት በቂ የሆነ ብርሃን መኖር አለበት

4.1.6 አማራጭ የሃይል ምንጭ (generator) ሊኖር ይገባል፡፡

4.1.7 ድርጅቱ ከማዘጋጃ ቤት የቧንቧ ውሃ ወይም አግባብ ባለው አካል ተመርምሮ ለሰው ልጅ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደ የጉድጓድ ወይም ከሌሎች ምንጭ የተገኘ ውሃ ሊኖረው ይገባል፡፡

4.1.8 ድርጅቱ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ጊዜያት በሙሉ መፀዳጃ ቤቱ ለተገልጋይ ክፍት መሆን አለበት፡፡

4.1.9 የወተቱን ይዘት ለማረጋገጥ የሚረዳ ላክቶሜትር (lacto- meter) መኖር አለበት፡፡

4.1.10 የሙቀት መለኪያ መሳሪያ ቴርሞሜትር መኖር አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

4.1.11 በመሸጫ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የመገልገያ ቁሳቁሶች ንፅህናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

4.1.12 በድርጅቱ ለወተትና ወተት ተዋፅዖ ማስቀመጫ ማቀዝቀዣ መኖር አለበት፡፡

4.1.13 የተሟላ የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ መስጫ መኖር አለበት፡፡

4.1.14 ማንኛውም ሰራተኛ ወደስራ ከመግባቱ በፊት ገላውን መታጠብ አለበት፣ ንፅህናውን የጠበቀ የስራ ልብስ በስራ ላይ ለብሶ መገኘት አለበት፡፡

4.1.15 ማንኛውም ደረቅ ቆሻሻ ከምንጩ (በስራ እንቅስቃሴ ከሚመነጭበት ቦታ) መሰብሰብ አለበት፡፡

4.1.16 መጨረሻ የተሰበሰበው ቆሻሻ በተገቢ መንገድ መወገድ አለበት፡፡

## 4.2. ዝርዝር መስፈርቶች

### 4.2.1 አካባቢያዊሁኔታ

4.2.1.1 ድርጅቱ ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ሊጣጣም የማይችልና በአገልግሎቱ ላይ የመበከል አደጋ ሊያስከትል ከሚችል ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ እና አምራች ድርጅት ቢያንስ 50 ሜትር መራቅ አለበት

4.2.1.2 ከቆሻሻ መጣያ ቢያንስ100 ሜትር መራቅ አለበት፡፡

### 4.2.2 የህንፃው ዲዛይንናግንባታ ሁኔታ

4.2.2.1 መስኮትና በሮች ተባይ፣ ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳት የማያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡

4.2.2.2 የአካል ውስንነት ላለባቸው የጋሪ መንቀሳቀሻ ምቹ የሆነ መወጣጫ (ራምፕ) መኖር አለበት

### 4.2.3 መፀዳጃ ቤት

4.2.3.1 የክፍሉ ጣሪያ ከፍታ ቢያንስ 2.4 ሜትር (ሁለት ነጥብ አራት ሜትር) ሊሆን ይገባል፡፡



©ESA

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

4.2.3.2 የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 1.2 ሜትር በ 1.2 ሜትር 1.44 ካ.ሜ. እና ከዚያ በላይ (አንድ ነጥብ ሁለት ሜትር በአንድ ነጥብ ሁለት ሜትር) የሆነ መሆን አለበት፡፡

4.2.3.3 በድርጅቱ ቢያንስ አንድ መፀዳጃ ቤት ሊኖር ይገባል፡፡

4.2.3.4 ከመፀዳጃ ቤቱ ቢበዛ በሶስት ሜትር ርቀት/በ15 ሰከንድ ሊደረስበት በሚችል/ አገልግሎት የሚሰጥ አግባብነት ያለው የእጅ መታጠቢያ ሊኖረው ይገባል፡፡

4.2.4 የድርጅቱ ሰራተኞች

4.2.4.1 ማንኛውም ከምግብና መጠጥ ዝግጅት ጋር፣ከምግብና መጠጥ እቃዎች ንክኪ ያላቸውና ምግብና መጠጥ የሚያጓጉዙ እና የሚያስተናግዱ ሰራተኞች በ3 ወራት ልዩነት የሚታደስ ከምግብ ወለድ በሽታዎች ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ የጤና ምርመራ ካርድ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

4.2.4.2 ሰራተኞቹ የምግብ ደህንነትና የአከባቢ ጤና አጠባበቅ ንፅህና ላይ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ስልጠና የወሰዱ መሆን አለባቸው፡፡

4.2.5 መሸጫ ክፍል

4.2.5.1 የክፍሉ ስፋት ቢያንስ 9ካሬ ሜትር ሆኖ የኮርኒሱ ከፍታ ቢያንስ ከወለሉ 2.4 ሜትር መሆን አለበት፡፡

4.2.5.2 ፓስቸራይዝድ የሆነ ወተት፣ የተለያዩ የእርጎ ውጤትች፣ ቅቤ፣ ከ1.67 ዲ.ሴ እስከ 4.4 ዲ.ሴ በሆነ የቅዝቃዜ መጠን መቀመጥ አለባቸው፡፡

4.2.5.3 ፓስቸራይዝድ በሆነ ወተት የተሰራ ቅቤ፣ አይብ እና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን ምርቶች ከ-18 ዲ.ሴ እና ከዚያ በታች በሆነ የቅዝቃዜ መጠን መቀመጥ አለባቸው፡፡

4.2.5.4 ፓስቸራይዝድ የሆነ እና ጥሬ ወተት ከተመረተ በሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

4.2.5.5 የተለያዩ የእርጎ ምርቶች ከተመረተ ከ7-10 ቀን ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

4.2.5.6 ቅቤ የተመጠበት የቅዝቃዜ መጠን ከ1.67 ዲ.ሴ እስከ 4.4 ዲ.ሴ ከሆነ በ15 ቀን ውስጥ፣ ከ-18 ዲ.ሴ እና ከዚያ በታች ከሆነ  በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

4.2.5.7 የማቀዝቀዣ ቅዝቃዜ መጠን የሚመዘገብበትየሙቀት መቆጣጠሪያ  ቼክ ሊስት ያለበት ሲሆን በቀን 2 ጊዜ በ12 ሠዓት ልዩነት ተመዝግቦ በማቀዝቀዣው ላይ ቅጹ ተሞልቶ በሌላ እስከሚተካ  ድረስ በሚታይ ቦታ ተለጥፎ መቆየት አለበት፡፡

### 4.2.6 የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ

4.2.6.1 የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የሚቀመጡበት ቦታ አካባቢ ንጽህናው የተጠበቀ ከተባይ፣ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳትን ነፃ መሆን አለበት

4.2.6.2 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማቆያ (garbage bin) ሶስት አራተኛው ሲሞላ ወደ ድርጅቱ አጠቃላይ መሰብሰቢያ ገንዳ መደፋት አለበት፡፡

4.2.6.3 ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰብሰቢያ ክዳን ያለውና በእግር ተረግጦ የሚከፈትና የሚዘጋ ጊዜያዊ እና በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማጠራቀሚያ/ማቆያ መኖር አለበት

4.2.6.4 የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች የሚቀመጡበት ቦታ አካባቢ ንጽህናው የተጠበቀ ከተባይ፣ከነፍሳት እና ከቆርጣሚ እንስሳት ነፃ መሆን አለበት፡

4.2.6.5 በተቋሙ የተለያዩ ቦታዎች የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች/መሰብሰቢያዎች መቀመጥ አለባቸው

4.2.6.6 ድርጅቱ የደረቅ ቆሻሻን በአይነት እና በባህሪያቸው በመለየት መሰብሰብና ማስወገድ አለበት (የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ)

4.2.6.7 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማቆያ (garbage bin) ሶስት አራተኛው ሲሞላ ወደ ድርጅቱ አጠቃላይ መሰብሰቢያ መገልበጥ አለበት፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD



©ESA

4.2.6.8 ድርጅቱ የመጨረሻ/አጠቃላይ የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ቦታ ላይ ከድርጅቱ ለሚመነጨው የደረቅ ቆሻሻ ተመጣጣኝ የሆነ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት

#### 4.2.7 የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

4.2.7.1 የፍሳሽ ቆሻሻን ለመሰብሰብ የሚጠቀመው የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ (ሴፕቲክ ታንክ) ከሆነ ሊሞላ 50 ሳንቲ ሜትር ሲቀረው መመጠጥ አለበት፡፡

#### 4.2.8 የምርት አቀባበል

4.2.8.1 መካከለኛ ቅዝቃዜ ለሚያስፈልጋቸው የቅዝቃዜ መጠኑ ከ4.4 ዲ.ሴ. በታች መሆን አለበት ፡፡

4.2.8.2 ከፍተኛ ቅዝቃዜ ለሚያስፈልጋቸው፡ የቅዝቃዜ መጠኑ ከ - 18 ዲግሪ እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

# 5 አካባቢያዊሁኔታ

5.1 ለጎርፍ፣ረግረጋማቦታናናዳተጋላጭመሆንየለበትም፡፡

5.2 ከነፍሳትመራቢያ፣ከቆሻሻመጣያ፣ከመጥፎሽታ፣ከኬሚካልወይምመርዝከሚከማችበትናበአጠቃላይምግብንሊበክሉከሚችሉናበሰውጤናናደህንነት ላይጉዳት ለሚያስከትሉ ነገሮች ተጋላጭ መሆን የለበትም፡፡

# 6 የህንፃውዲዛይንናግንባታሁኔታ

6.1 የህንፃው ዲዛይንና ግንባታ ላይ መጨመር ያለባቸው የፍሳሽ፣የኤሌክትሪክ፣የውሃ፣ እና ሌሎች መሰመሮች ዝርጋት የአመራረት ሂደቱን ሊበክል በሚችል አግባብ መሆን የለበትም

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

6.2 የክፍሉ ስፋት ድርጅቱ እንደሚሰጠው አገልግሎት መጠን በቂ ሆኖ በአገልግሎቱም ላይ የመበከል፣ የመመረዝ እና የመደበላለቅ ሁኔታ የማያመጣ ሆኖ ስራውን በትክክል ሊያሰራ በሚያስችል መልኩ የተሰራ መሆን አለበት፡፡

6.3 የድርጅቱ ህንፃውም ሆነ በውስጡ ያሉት ክፍሎች የመሠረቱ አሠራር ውሃን፣ ተባይ፣ነፍሳት እና ቆርጣሚ እንስሳትን የማያስገባ መሆን አለበት፡፡

6.4 የድርጅቱ ህንጻ ያረፈበት ቦታ አፈር ዝናብም ሆነ ጎርፍ በቀላሉ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

6.5 መስኮቶችና በሮች በቀላሉ መከፈትና መዘጋት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

6.6 ወለሉ ለማፅዳት የሚያመች ያልተሰነጣጠቀና የማያዳልጥና በቀላሉ ሊታጠብ የሚችልና ውሃ የማያቁር መሆን አለበት፡፡

6.7 ግድግዳው ለማፅዳት የሚያመች ፈካ ያለ ወይም ነጭ ቀለም የተቀባ ያልተሰነጣጠቀ መሆን አለበት

6.8 ኮርኒሱ ለማፅዳት የሚያመች፣ ነጭ ቀለም የተቀባ ያልተከፈተ/ያልተቀደደ፣ ሙቀትን መቋቋም መሆን አለበት

7.የውሃ አቅርቦት

7.1 በድርጅቱ የሚዘረጉ የውሃ ማከፋፈያ መስመሮች ሙሉ በሙሉ የመሰበር/የመሰንጠቅ ችግር የሌላቸውና የማያፈሱ ወይም ስርገት የሌላቸው መሆን አለባቸው

7.2 የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚ እቃከፕላስቲክ ወይም ከፋይበር ግላስ (fiber glass) የተመረተ መሆን አለበት

7.3 የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያ ጋን/እቃ ውሃ በሚቋረጥበት ወቅት የመያዝ አቅሙ ቢያንስ ለሁለት ቀንና ከዚያ በላይ ማገልገል የሚችል መሆን አለበት

7.4 የመጠባበቂያ ውሃ ማጠራቀሚያ ጋን/እቃ በየጊዜው መጸዳት እና በውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች መታከም አለበት፡፡

# 8 የመፀዳጃ ቤት

8.1 የክፍሉ ወለል እና ግድግዳ መታጠብ፣ መፅዳት የሚችል፣ በውሃ የማይቦረቦር እና ልስላሴ ካለው የግንባታ ቁሳቁስ መሰራት አለበት፤

8.2 መፀዳጃ ቤቱ በድርጅቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተሰራ መኖር አለበት

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

©ESA

8.3 ክፍሉ ንፅህናው የተጠበቀ መሆን አለበት

8.4 ከመጥፎ ሽታ ነፃ መሆን አለበት

8.5 የክፍሉ በር በቀላሉ ከውስጥ በኩል መከፈትና መዘጋት የሚችል መሆን አለበት

8.6 የመጸዳጃ ቤቱ መቀመጫ በውሃ ግፊት የሚሰራ/ሽታ አልባ መጸዳጃ ቤት መሆን አለበት፤

8.7 መጸዳጃ ቤት ውሰጥ ክዳን ያለውና በእግር ሲረገጥ የሚከፈትና የሚዘጋ ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት

8.8 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሶች የተሰራ ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባትም ሆነ ማስወጣት የማይችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

8.9 የእጅ መታጠቢያ በግድግዳ ላይ የተገጠመ ሲንክ/ገንዳ ከወራጅ ውሃ ጋር የተየያያዘ መሆን አለበት፡፡

8.10 ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን ደረቅ ወይም ፈሳሽ ሳሙና መኖር አለበት

8.11 የፍሳሽ መስመሩ ከመጸዳጃ ቤቱ ከወጣ በኋላ የመፈተሻ ባለክዳን ቀዳዳ (man-hole) መኖር አለበት፡፡

## 9 የሰራተኞች የስራ ደህንነት መጠበቂያ ቁሶች፣የትምህርት ደረጃና ስልጠና፣የጤና ምርመራ

9.1 ሰራተኞችበድርጅቱ ውስጥ በስራ ላይ ባሉበት ወቅት የስራ ልብስና ቆብ ያላቸውእና የግል ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆን አለባቸዉ፡፡

9.2 ሰራተኞች ጥፍራቸው ያጠረ፣የጥፍር ቀለም ያልተቀቡ፣ጸጉራቸው የተሸፈነ፣የተለያዩ ጌጣጌጥ በጣታቸው ላይ ያላደረጉ ከጋብቻ ቀለበት በስተቀር በእጃቸው ላይ ምንም አይነት ቁስል የሌለባቸው መሆን አለባቸው፡፡

## 10 መሸጫ ክፍል

10.1 ክዳን ያለው በእግር ተረግጦ የሚከፈትናየሚዘጋ እና አግባብነት ያለው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ መኖር አለበት

10.2 የወተት መያዣ ወይም ማከፋፈያ ዕቃዎች ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡

10.3 የዕቃዎች ማስቀመጫ በቀላሉ ሊፀዳ የሚችል መዝጊያ ያለው መደርደሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

10.4 የሚሰራ በቅርብ ጊዜ የታደሰ በካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ጋዝ የተሞላና እሳት አደጋ ማጥፊያ መኖር አለበት፡፡

## 11. የወተት እቃ ማጠቢያ

11.1 ቦታው እጥበቱን ለሚያከናውነው ሠራተኛ እንቅስቃሴ ምቹ መሆን አለበት

11.2 ባለሶስት ጉድጓድ ሲንክ/መዘፍዘፊያ/ ከዕቃዎቹ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መዘጋጀት አለበት

11.3 የማጠቢያ ውሃ የባንባ ውሃ መኖር አለበት፡፡

11.4 ለዕጥበት የሚያገለግሉ ሳሙናዎችና ኬሚካሎች መሟላት አለባቸዉ፡፡

11.5 የታጠቡ ዕቃዎች እንዲደርቁ ማንጠፍጠፊያ ከፕላስቲክ (የማይበሰብስና ዝገትን መቋቋምየሚችል) ማቴሪያል የተሰራ ራክ መኖር አለበት

11.6 ለታጠቡ ዕቃዎች ማስቀመጫ መደርደሪያ መኖር አለበት፡፡

11.7 እጥበቱስድስቱንም የአስተጣጠብ ሂደት የሚከተል መሆን አለበት፡፡

## 12. የግል ንፅህና

እጅን አንደአስፈላጊነቱ በየጊዜው በሳሙና ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መታጠብ ያስፈልጋል፡-

12.1 ከመጸዳጃ ቤት መልስ

12.2 በስራ መሃል ከተወስደ ዕረፍትመልስ

12.3 ማንኛውንም የሰውነት አካል በስራ መሃል ከተነካ በኋላ

12.4 ቆሻሻ ወይም ማንኛውም የማጽጃ ቁሳቁስና ኬሚካሎች ከተነካ በኋላ

12.5 ማንኛውንም የጽዳት ስራ ከተከናወነ በኋላ

## 13 የደረቅ ቆሻሻአሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ

13.1 ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ የመሰብሰቢያ ክዳን ያለውና በእግር የሚከፈትና የሚዘጋ ጊዜያዊ እና በቦታው ከሚመነጨው የቆሻሻ መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ማጠራቀሚያ/ማቆያ መኖር አለበት

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

 ©ESA

13.2 የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዝገትን መቋቋም ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተሰራ፤በቀላሉ ማንቀሳቀስ የሚቻል፤ለማጽዳት አመቺ የሆኑ፤ ፍሳሽ ማስገባ;ትም ሆነ ማስወጣት የማይችሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

13.3 የደረቅ ቆሻሻን በአይነት እና በባህሪያቸው (የሚበሰብሱ እና የማይበሰብሱ) በመለየትበመሰብሰብ እና ማስወገድ አለበት፡፡

13.4 በንግድ ቤቱ ደረቅ ቆሻሻ ተሰባስቦ ወደ ሚወገድበት ስፍራ እስከሚወሰድ ድረስ አግባብነት ያለው የመጨረሻ የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ክዳን ያለው እቃና ቦታ ሊኖር ይገባል

## 14 የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

14.1 ድርጅቱ በአግባቡ የተሰራ( በፕላን የተዘረጋ ፤ ከእይታ የተሸፈነ፣ ፍሳሽ የሌለው) የፍሳሽ ቆሻሻ መስመር ሊኖረው ይገባል ፡፡

14.2 አገልግሎት (ከዕቃ ማጠቢያ፣ ከዕጅ መታጠቢያና ከመጸዳጃ ቤት ) የሚመነጭ ማንኛውም ፍሳሽ ቆሻሻ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ በተሰራ የፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ወይም ከተፈቀደ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ጋር መገናኘት አለበት

14.3 ማንኛውም የፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ዝናብ ውሃ ማስወገጃ መስመር ወይም ወደ አካባቢ መለቀቅ የለበትም

14.4 የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የሚመለከተው አካል ሲጠይቅከተፈቀደ የፍሳሽ መስመር ጋር የተያያዘበት፤የተጠራቀመ ፍሳሽ የተመጠጠበትመረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል

# 15 የምርትአቀባበል

15.1 ወደ ወተትና፣ የወተት ተዋፅኦ መሸጫው የሚገቡ ምርቶች መለያ/Label/ አጠቃላይ የምርቱ መረጃ (ስም፣ በውስጡ ያለው ይዘት ፣ያምራቹ አድራሻ)፣ የተመረተበትን ሀገር፣ያመረተው ድርጅት፣ የተመረተበት ጊዜና የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ ተረጋግጦ ድርጅቱ መረከብ አለበት፡፡

15.2 ርክክብ ሚደረጉ የወተትና ፣የወተት ተዋፅኦ ምርቶች የሙቀትና የቅዝቃዜ መጠናቸው መለካት አለበት፣

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

15.3 ድርጅቱ ጥሬ ወተት የሚረከብ ከሆነ ለመረከቢያነት የሚያገለግል አግባብነት ያለው እቃ (በወተቱ ላይ የመበከል ወይም ይዘቱን የመቀየር ባህሪ የሌለው ‘stainless steel’ (food graded) መሆን አለበት፡፡

15.4 ቀድሞ የገባ ወተት እና የወተት ተዋጽኦ ቀድሞ መውጣት አለበት፡፡

## 16 የሲጋራማጨስንበተመለከተ

16.1 ድርጅቱ ሲጋራ ማጨስ የሚከለከልበትን አዋጅ መተግበር አለበት

**እዝል ሀ**

**የወተት እቃ የአስተጣጠብ ሂደት**

ቅድመ ዕጥበት፡- የተራረፉ ምግቦችን ማራገፍ

ዕጥበት፡- በሞቀ ውሃ ሳሙናዎችንና ኬሚካሎችን በመጠቀም ቅባትና ቆሻሻን ማጠብ፤አስፈላጊ ከሆነ በማጠቢያ ኬሚካሎች ከ2-3 ደቂቃ መዘፍዘፍ

ማለቅለቅ፡- የቀሩ ቆሻሻዎችንና አረፋዎችን በወራጅ ውሃ ማለቅለቅ

ማጽዳት፡- በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን በሚገድል ኬሚካል ማጽዳት

የመጨረሻ ማለቅለቅ፡- በወራጅ ውሃ በሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ገዳይ ኬሚካሉን ማጽዳት

ማድረቅ፡- በአየር እንዲደርቅ በማንጠፍጠፊያ /ራክ/ ላይ ወይም በማድረቂያ ማሽን በማድረግ ማድረቅ

የታጠቡ እቃዎች ማስቀመጫ መዝጊያ ያለው በቀላሉ ሊጸዳ ከሚችል ለስላሳ ጣውላ ወይም ከማይዝግ ብረት የተሰራ መደርደሪያ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD



©ESA

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ
Ethiopian Standards Agency

DRAFT ETHIOPIAN STANDARD

## *Organization and Objectives*

The Ethiopian Standards Agency (ESA) is the national standards body of Ethiopia established in 2010 based on regulation No. 193/2010.ESA is established due to the restructuring of Quality and Standards Authority of Ethiopia (QSAE) which was established in 1998.

***ESA's objectives are:-***

- ❖ Develop Ethiopian standards and establish a system that enable to check whether goods and services are in compliance with the required standards,
- ❖ Facilitate the country's technology transfer through the use of standards,
- ❖ Develop national standards for local products and services so as to make them competitive in the international market.

## Ethiopian Standards

The Ethiopian Standards are developed by national technical committees which are composed of different stakeholders consisting of educational Institutions, research institutes, government organizations, certification, inspection, and testing organizations, regulatory bodies, consumer association etc. The requirements and/ or recommendations contained in Ethiopian Standards are consensus based that reflects the interest of the TC representatives and also of comments received from the public and other sources. Ethiopian Standards are approved by the National Standardization Council and are kept under continuous review after publication and updated regularly to take account of latest scientific and technological changes.
Orders for all Ethiopian Standards, International Standard and ASTM standards, including electronic versions, should be addressed to the Documentation and Publication Team at the Head office and Branch (Liaisons) offices. A catalogue of Ethiopian Standards is also available freely and can be accessed in from our website.

ESA has the copyright of all its publications. No part of these publications may be reproduced in any form without the prior permission in writing of ESA.
International Involvement
ESA, representing Ethiopia, is a member of the International Organization for Standardization (ISO), and Codex Alimentarius Commission (CODEX). It also maintains close working relations with the International Electro-technical Commission (IEC) and American Society for Testing and Materials (ASTM).It is a founding member of the African Regional Organization for standardization (ARSO).

***More Information?***
***Contact us at the following address.***
***The Head Office of ESA is at Addis Ababa.***

☎ ***011- 646 06 85, 011- 646 05 65***
***011-646 08 80***
🖂 ***2310 Addis Ababa, Ethiopia***
***E-mail: info@ethiostandards.org,***
***Website: www.ethiostandards.org***

**Standard Mark**